DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of the Chancellor

ነሀሴ (August) 2018

ውድ ወላጆች፣

ስለ ተማሪ እና ስለ ትምህርት ቤት የእድገት እርምጃ የበለጠ ለማወቅ እንድንችል በየፀደዩ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት ተማ ሪዎች ዓመታዊ የግምገማ ፈተና ይፈተናሉ። ይህ የግምገማ ፈተና፣ PARCC በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህም ለኮሌጅ እና ለሙያ ዝግጁነትን የሚያመለክት የመለኪያ ቅንጅት (The Partnership for Assessment of Readiness for College and Career) በመባል ይታወቃል።

የስቴቱ የትምህርት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ጽሕፈት ቤት (OSSE)፣ በ 2017-2018 የትምህርት ዓመት በነሀሴ (August) አጋ ማሽ ላይ የ OSSE ፈተና ውጤቶችን ይፋ አድርጓል። ከ OSSE ተያይዞ የቀረበው ዘገባ የልጅዎን የግል የፈተና ውጤቶች ይዘረዝራል።

በ 2017-2018 የትምህርት ዓመት የዲሲፒኤስ (DCPS) ተማሪዎች በ PARCC ግምገማ ቀጣይነት ያለው የማያቋርጥ እድገት ያመጡ መሆናቸውን ስግልጽላችሁ ደስ እያለኝ ነው። ተማሪዎቻችንን በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ፣ ቀጠና፣ እና በተማሪ ምድብ ቡድን ውስጥም ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የከተማችን አቃላይ ውጤት የላቀ ደረጃ ላይ ሊገኝ ችሏል። አብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች በንባብ እና በሂሳብ በሁለቱም የላቀ ከፍተኛ ውጤት ሊያመጡ ችለዋል። እነዚህ መሻሻሎች የልጆች የት ምህርት ታታሪነት እና የመምህራኖቻቸው ጥረቶች እና እንዲሁም የእርስዎ ድጋፍ ጭምር ውጤቶች ናቸው።

በዲስትሪክታችን የ PARCC እድገት ተደስተናል፤ ሆኖም ልጆች ሁሉ ለወደፊቱ የተዘጋጁ ሆነው እንዲገኙ ከወዲሁ ማከናወን የሚገቡን ሥራዎች አሉ። በዚህ ዓመት ልጅዎም ሆነ የልጅዎ ትምህርት ቤት የተፈለገውን ያህል ያከናወነ ቢሆንም፣ ቀጣይ ነት ባለው ሁኔታ እያሻሻለ መዳዙን ዕውን ለማድረግ ዲሲፒኤስ ጠንክሮ እየሠራ ነው።

የ PARCC ፈተና በጣም ጠቃሚ ነው፣ ይሁን እንጅ የሚመዝነው አንድ ዐይነት ክህሎት ብቻ ነው። የልጅዎን የተሟላ እና የተጠቃለለ ገጽታ ለማግኘት በአንድ ነጠላ ፈተና ላይ ብቻ አናተኩርም። በመሆኑም፣ ከእርስዎ ጋር እንዴት አብረን ለመሥራት እና ልጅዎ ታታሪ እንዲሆን ለመርዳት፣ የትምህርት ውጤቶችን፣ የመምህራን ሪፖርቶችን፣ ከትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን፣ ተማሪዎች ስለ ትምህርት ቤት ምን እንደሚሰማቸው፣ እና ሌሎችንም በርካታ ጉዳዮችን በማካተት እንመለከታለን።

የ PARCC የፈተና ውጤቶቻችን እና የተማሪዎቻችን የወደፊት እጣ እድል ከዚህ በመነሣት ብቻ እንደሚያድጉ እርግጠኛ ነኝ። በልጅዎ ትምህርት ጉዳይ ተጓዳኛችን በመሆንዎ እናመሰግንዎታለን።

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፣

Amanda Alexander
ጊዜያዊ ቻንስለር፣ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች
(Interim Chancellor, DC Public Schools)